# የመፈንቅለ መንግሥት ጽንሰ ሃሳብ እና መገለጫዎች (the concept of coup d'état)

## መግቢያ

መፈንቅለ መንግሥት ከጥንታዊ የሥልጣኔ ባለቤት ሃገራት ጀምሮ በታሪክ የሚታወቅ ሕዝብን እየመራ ባለ የመንግሥት ወይም የገዢ አካል ላይ የሚደረግ ከሥልጣን የማዉረድ ሁኔታ ሲሆን የበርካታ ሃገራት የታሪክ አካልም ነዉ፡፡

ለዚህ ጽሑፍ ዋነኛ መነሻ የሆነዉ የመፈንቅለ መንግሥት ጽንሰ ሃሳብ እና ትርጓሜዉ በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ የሚሰጠዉ ትንታኔ ከምን አንጻር የታየ እንደሆነ በዉል ባይታወቅም አብዛኞቹ ይህን መሰል ድርጊቶች መፈንቅለ መንግሥት ነዉ የሚል ስያሜ ሲሰጣቸዉ እንመለከታለን፡፡

የመፈንቅለ መንግሥት ጽንሰ ሃሳብ ምንድነዉ? መገለጫዎቹ ምን ምንድናቸዉ? የአፍሪካ ኅብረት የሕግ ማዕቀፍ ምን ይላል? በፌደራላዊ የመንግሥት ሥርዓት ተከታይ ሃገራት በፌዴሬሽኑ አባላት ዉስጥ የሚከናወኑ የሥልጣን ቅምያ ሙከራዎችንስ መፈንቅለ መንግሥት ልንላቸዉ ይቻላል? እንመልከት፡፡

## የመፈንቅለ መንግሥት ጽንሰ ሃሳብ

መፈንቅለ መንግሥት ወይም በእንግሊዘኛ መጠሪያዉ coup d'etat ከፈረንሳይ የተወሰደ ቃል ሲሆን ፍቺዉም blowing state ወይም መንግሥትን መበታተን የሚለዉን ትርጓሜ የያዘ እንደሆነ መጽሃፊት ያስቀምጣሉ፡፡ ይኸዉም በሥልጣን ላይ ያለን መንግሥት ወይም ገዢ በጉልበት ሳይታሰብ ከሥልጣን መጣል መሆኑን እንደሚያመላክት ያስረዳሉ፡፡ ይሁን እንጂ ምንም እንኳን ከላይ የተጠቀሰዉን የፈረንሳይኛ ፍቺ የያዘ ቢሆንም በበርካታ ጽሁፎች እና መሰል ሰነዶች ላይ ወጥ እና ተመሳሳይ አይነት ትርጉም ማግኘት ያስቸግራል፡፡ የኢንሳይክሎፒዲያ ብሪታኒካ መዝገበ ቃል 2ኛዉ ዕትም በተመሳሳይ ሁኔታ ቃሉን ሲተረጉም በሥልጣን ላይ ያለን መንግሥት አነስተኛ በሆነ ቡድን ወይም አካል በድንገት ከሥልጣን ማዉረድ ነዉ በሚል ይፈታዋል፡፡

*"Coup d'état, also called coup, the sudden, violent overthrow of an existing government by a small group.[1]."*

በዘመናዊ የመፈንቅለ መንግሥት ታሪክ የ1799ኙ የፈረንሳዩ ናፖሊዎን መፈንቅለ መንግሥት እንዲሁም የ1851ዱ የሉዊስ ናፖሊዎን በቀዳሚነት ይጠቀሳሉ፡፡ ከዚህ ባለፈ ከ20ኛዉ ክፍለ ዘመን ጀምሮም በደቡብ አሜሪካ ፣ በእስያ እና በአፍሪካ መፈንቅለ መንግሥት ባሕሪዉን እና መገለጫዉን እቀየረ እየተበራከተ መምጣቱን መመልከት ይቻላል፡፡ በተለይ በደቡብ አሜሪካ እና እስያ ከቀዝቃዛዉ የዓለም ጦርነት ጋር ተያይዞ በአፍሪካ ደግሞ ከቀኝ ግዛት ነጻነት ማግስት በአህጉሪትዋ በስፋት ታይቷል፡፡ በአለም ባንክ የ1991 የዓለም እድገት ሪፖርት መሰረትም እያደጉ ባሉ ሃገራት በአማካይ በአምስት አመት ዉስጥ አንድ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ እንደሚካሄድ በተቋሙ ሪፖርት ሰፍሯል፡፡

## መፈንቅለ መንግሰት በምን ይገለጻል?

ከላይ ከተቀመጡት ትርጓሜ በመነሳት ምንም እንኳን ወጥ የሆነ የጉዳዩ ጽንሰ ሃሳብ ሰፈሮ እና ተተንትኖ ባይገኝም ካሉት ሰነዶች በመነሳት መፈንቅለ መንግሥት በምን ይገለጻል ወይም መፈንቅለ መንግሰት ልንል የምንችለዉ ምን ምን ነጥቦች ሲሟሉ ነዉ የሚለዉን ከተለያዩ ዕይታዎች የጋራ የሆኑ ሶስት ነጥቦችን እንመልከት፡-

**1ኛ. የፖለቲካ ቡድን ወይም የሽምቅ ተዋጊ (existence of a small group or political faction or military power)**

መፈንቅለ መንግሰት ተደርጓል ወይም ደግሞ ድርጊቱ መፈንቅለ መንግሰት ነዉ የሚለዉን ስያሜ ለማግኘት በቀዳሚነት መኖር እንዳለበት የሚጠበቅ ነጥብ የድርጊቱን ዉጤት የሚፈልግ ወይም ድርጊቱ ከተሳካ በኋላ ያሰበዉን ለማስፈጸም የተዘጋጀ ወይም ለመፈጽም ያቀደ አካል መኖር ነዉ፡፡ ይህ አካል ወይም ቡድን ብለን ልንጠራዉ የምንችለዉ በመንግሥት መዋቅር ዉስጥ አልያም ከመዋቅር ዉጭ ያለ የፖለቲካ ቡድን፣ የሽምቅ ተዋቂ ወይም ወታደራዊ ሃይል ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ ሃይል በተለምዶ በረጅም ወይም በአጭር ግዜ እቅድ መንግሰትን ለመጣል ያሰበ በህቡዕ የተደራጀ ሃይል ነዉ፡፡ ይህ

[1] Political intervention, written by: The Editors of Encyclopaedia Britannica, 2nd edition

አካል ሳይኖር ወይም ተደራጅቶ ያቀደዉ እቅድ ሳይኖር መንግሰት ግልበጣን ማሰብ ከባድ እና አዳጋች ነዉ፡፡

## 2ኛ. ሃይልን መጠቀም

ድርጊቱ በሚፈጸምበት ወቅት ዋነኛ ማሳኪያ ተደርጎ በበርካታ የመፈንቅል መንግሰት ክንዉኖች ዉስጥ የሚወሰደዉ በሁለተኛ ደረጃ የሚታይ መሰረታዊ ነጥብ ሃይልን መጠቀም ሲሆን ይህም በከፊል ወይም በሙሉ ሉዓላዊ በሆነች ሃገር ያለን የመከላከያ ወይም የፖሊስ ወይም የደህንነት መዋቅር መቆጣጠር እንደሆነ በርካታ ጽሁፎች ይስማሙበታል፡፡ እንደ ኢንሳይክሎፒድያ ትንተናም ጉልበትን መጠቀም ከቀዳሚ ሁኔታዎች አንዱ እንደሆን ያሰቀምጣል፡፡

*". . . the chief prerequisite for a coup is control of all or part of the armed forces, the police, and other military elements.[2]"*

ከዚህ በተጨማሪ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት በ36ኛዉ የሎሜ መደበኛ ጉባኤ[3] "ኢ-ህገ መንግሰታዊ የመንግሥት ለዉጥን" (OAU response on un constitutional change of government) እና የአህጉሪቱን የፖለቲካ ለዉጦች በተለይም የዲሞክራሲ ግንባታ አስመልክቶ ተወያይቶ ባስቀመጠዉ ማዕቀፍ መፈንቅለ መንግሥት የሚለዉን ስያሜ "ህገ-መንግሰታዊ አካሄድን ያልተከተለ የመንግሰት ለዉጥ" ብሎ አቻ መጠሪያ የሰጠዉ ሲሆን ልክ እንደሌሎቹ ሁሉ ወታደራዊ ሃይልን በመጠቀም በዲሞክራሲያዊ መንገድ የተመረጠን ዕውቅና ያለዉ መንግሥት መጣል የመጀመሪያዉ የመፈንቅለ መንግሰት መገለጫ ወይም ድርጊቱ መፈንቅለ መንግሰት ነዉ ተብሎ እንዲጠራ እንደሚያደርገዉ አስቀምጧል፡፡ ከድርጅቱ ማዕቀፍ አንጻር በዴሞክራሲያዊ መንገድ የተመረጠን መንግሥት ብቻ ብሎ ማሰቀመጡ ዲሞክራሲያዊ ምርጫን ባልተከተለ ሁኔታ ወደ ሥልጣን መጥተዉ በመንግሥት ግልበጣ በሃይል የተገረሰሱ መንግሥታት የወረዱበትን መንገድ መፈንቅለ

---

[2] *Ibid*

[3] Lomé Declaration of July 2000 on the framework for an OAU response to unconstitutional changes of government (AHG/Decl.5 (XXXVI)

መንግሰት አይደልም የሚል ፍቺ የሚሰጥ በመሆኑ ትርጓሜዉን ያጠበበና በዴሞክራሲያዊ መንገድ ብቻ የሚመረጡ መንግሰታት ላይ የሚቃጣን ድርጊት ከላል የሚሰጥ እንደ ሆነ መረዳት ይቻላል፡፡

በመሆኑም ከላይ በተቀመጠዉ መሰረት ሃይልን መጠቀም ሌላዉ ዋነኛ ሁኔታ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

**3ኛ. ድንገታዊነት** (it is a sudden act)

በዓለም ላይ የተከናወኑ የተሳኩ ወይም ያልተሳኩ የመንግሥት ግልበጣዎች በታሪክ እንደሚያሳዩት ድርጊቱ ተወጥኖ እሰኪፈጸም ድረስ በህቡዕ በተደራጀ ሃይል በድንገት የሚፈጸም መሆኑን ነዉ፡፡ ይህም መፈንቅለ መንግሥቱ እንደሚከናወን ግንዛቤ ያላቸዉ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የሚያዉቁ የቡድኑ አባላት በታቀደዉ ግዜ ለመፈጸም የሚያሰችላቸዉን ዝግጅት ካጠናቀቁ በኋላ በሥልጣን ላይ ያለዉን መንግሰት ያወርዱታል፡፡ ይህንን በርካቶች እንደ አንደ መስፈርት የሚወስዱት ቢሆንም እንኳን ይህ ቅድመ ሁኔታ በሽምቅ ዉጊያ በረጅም ግዜ ሂደት ወደ ከተማ በመግባት ሥልጣን የሚይዙ ሃይሎችን ከላይ በተጠቀሰዉ መልኩ አካቶ ያስረዳል ወይ ብለን የተመለከትን ከሆነ አጠያያቂ ነዉ፡፡

ይሁንና በርካቶች እንደሚስማሙበት እና እንደሚያሰቀምጡት ሽምቅ ተዋጊዎችም ቢሆን ወደ ከተማ ገብተዉ ሥልጣን የሚቆጣጠሩበት ሁኔታ ድብቅነትና ድንገተኝነቱ ከላይ ከተቀመጡት አንጻር ሙሉ ለሙሉ ባይሆንም በተወሰነ መልኩ መሆኑ አይቀሬ ስለሆነ ድንገተኛነቱን ( the sudden act) እንደ አንድ መንግሥት ግልበጣ መገለጫ ወይም ቅድመ ሁኔታ መቆጠር የማይቀር ነዉ ብለዉ ይመለከቱታል፡፡

**የተለየዉ የአፍሪካ ህብረት ዕይታ**

ከላይ በዚህ ጽሑፍ መግቢያ ላይ እንደሰፈረዉ መፈንቅለ መንግሰት የዓለማችን አንዱ የሃገራት የፖለቲካ ታሪክ ሆኖ የቀጠለ ሲሆን በዘመናዊ የሰዉ ልጅ የሕዝብ አስተዳደር በተለይም ከሁለቱ የዓለም ጦርነቶች እና ከቀዝቃዛዉ የዓለም ጦርነት በኋላ የተለመደ ሆኖ ቆይቷል፡፡

ይህ የመንግሥት ሥርዓት ግልበጣ መልኩ እና ባህሪዉ ከሃገራት ሃገራት የተለያየ ቢሆንም በአፍሪካ የተከናወኑ በርካታ የመንግሥት ግልበጣዎች የሚያመሳስላቸዉ ጉዳዮች አሉ፡፡ አህጉሪቱን ከቀኝ ግዛት ለማላቀቅ ሲደረጉ የነበሩ ትግሎችን እንደ መነሻ ወስደን ያየን እንደሆነ ከቀኝ ገዢዎቻቸዉ ነጻ የወጡ ሃገራት የመሰረቷቸዉ መንግሰታት እና እነሱን የተኩ በርካቶች በዚሁ የመንግሰት ምሰረታ የተዋቀሩ ናቸዉ፡፡

በዚህ መሰርት ከላይ የተቀመጡ ነጥቦች እንደተጠበቁ ሆኖ የቀደሞዉ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የአሁኑ የአፍሪካ ህብረት በሃይል የሚደረግ የመንግሰት ግልበጣን “ Un constitutional change of government’’ በሚል ስያሜ ከመስጠት ባሻገር መፈንቅለ መንግሰት የሚለዉን ጽንሰ ሃሳብ ዕዉቅና የሰጠበት አግባብ ለየት ያሉ አህጉራዊ እይታዎች አሉት፡፡ ድርጊቱን ከዴሞክራሲያዊ ሃገር ግንባታ ጋር የሚያይዘዉ ህብረቱ የሚከተሉትን ነጥቦች ያስቀምጣል፡-

*In order to give practical effect to the principles we have enunciated, we have agreed on the following definition of situations that could be considered as situations of unconstitutional change of government:*

I. *military coup d'etat against a democratically elected Government;*
II. *intervention by mercenaries to replace a democratically elected Government;*
III. *replacement of democratically elected Governments by armed dissident groups and rebel movements;*
IV. *the refusal by an incumbent government to relinquish power to the winning party after free, fair and regular elections.*

ህብረቱ ካሰቀመጠዉ ነጥቦች አንጻር ሁለት ለየት ያሉ ምልከታዎችን አካቷል፡-

1ኛ. ድርጊቱ የሚፈጸመዉ በወታደራዊ አካል ወይም ሃይል ብቻ መሆኑ እና

2ኛ. በህገ-መንግሰታዊ ሥርዓቱ መሰረት ነጻ፣ ገለልተኛ እና በግዜ ገደቡ መሰረት በተከናወነ ምርጫ ላሸነፈ አካል ሥልጣንን አለቀም ማለተንም እንደ መፈንቅለ መንግሰት የሚቆጥረዉ መሆኑን ነዉ፡፡ ከዚህ ባለፈም በሁለተኝነት ያሰቀመጠዉ (*intervention by mercenaries to replace a democratically elected ገovernment)* እንደ ማሊ ያሉ ሃገራት በዉጭ

ሃገራት ሙሉ ድጋፍ ከሥልጣን የወረዱ የቶማስ ሳንካራ ዓይነት የመንግሰት ግልበጣዎችም በመንግሰት ግልበጣነት ዕዉቅና የሚሰጥ ይመስላል፡፡

ከላይ በተቀመጠዉ ሃሳብ መሰረት ህብረቱ መፈንቅል መንግሥት ተከናዉኗል ብሎ ሊያመንባቸዉ የሚችልባቸዉ ጉዮች በዚህ መልኩ የተገደቡ መሆናቸዉ ምናልባትም ህገ-መንግሰት ሳይኖራቸዉ ወደ ሥልጣን የወጡ በርካታ የአህጉሪቱን መንግሰታት፣ የቀድሞ ቡድኖች ወይም ሽምቅ ተዋጊዎች እንዲሁም በዴሞክራሲያዊ መንገድ የተሸነፉ መንግሥታትን በሃይል ከሥልጣን ለማዉረድ የሚደረግዉ ሁኔታስ እንዴት ያየዋል ለሚለዉ ህብረቱ በዝርዝር ያስቀመጠዉ እና እየተተገበረ ያለ ምላሽ ሊሰጥ የሚችል ነገር የለም፡፡

## ማጠቃለያ

መፈንቅል መንግሰት ወይም የአፍሪካ ህብረት እንዲመያስቀምጠዉ ህገ-መንግሰታዊ አካሄድን ባልተከተለ መልኩ ሥልጣን ለመያዝ መሞከር ወይም መያዝ የሚለዉ ጽንሰ ሃሳብ በበርካታ ጽሁፎች እና ዘገባዎች የድርጊቱን መስፈርት ወይም መገለጫዎቹ ምን እንደሆኑ በዝርዝር ሳይታወቅ መፈንቅለ መንግሰት ወይም የመንግሰት ግልበጣ ብሎ መሰየም የተለመደ ሆኗል፡፡ ምንም እንኳን ወጥ፣ ያለቀለት ትርጓሜና መገለጫ የተቀመጠለት ባይሆንም ጽንሰ ሃሳቡ ምን ምን ነጥቦችን በአማዛኙ ሲያሟላ መንግሰት ግልበጣ የሚለዉ ስያሜ ሊሰጠዉ እንደሚገባ እንደመነሻ ለማብራራት ተሞክሯል፡፡ ስለሆነም ጽንሰ ሃሳቡን ከላይ ከተቀመጡት መገለጫዎች ዉጭ የሚከናወኑ ድርጊቶችን ሁሉ መፈንቅለ መንግሰት ነዉ ብሎ መቀበል አስቸጋሪ ከመሆኑ ባለፈ ስያሜዉን ተከትሎ የሚያመጡት አሉታዊ የሃገራት የዉስጥ ፖለቲካ ቀዉስ በርካታ ነዉ፡፡

በሃገራችን ነባራዊ ሁኔታም ከዚህ ቀደም በአህዳዊ የመንግሰት ሥርዓት ግዚያቶች ከተከሰቱት የመንግሥት ግልበጣ ባህሪያቶች አንጻር ሲታይ እየተከተልን ካለዉ የመንግሰት ሥርዓት በፌዴሬሽኑ አባል ሃገራት የዉስጥ ችግሮችን እና የሚፈጠሩ ቀዉሶችን መፈንቅለ መንግሰት የሚል ስያሜ ሲሰጣቸዉ ይታያል፡፡ ይሁን እንጂ በጽሁፉ ከተዘረዘሩት መነሻዎች አንጻር በሶስቱ መገለጫዎች ድርጊቶቹን ስንመዘን የማያሟሉ ነጥቦች እንዳሉ መመልከት ይቻላል፡፡ ከዚህም ባለፈ ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግሰት የመንግሥት አዋቃቀር መንፈስ በመነሳት የሃገርን ቁመና ይዞ ያለዉ የፌደራል መንግሰት ሥልጣን ህልዉና አደጋ

ላይ ሳይወድቅ እና ለሃገርም ስጋት ሆኖ ሊታይ የሚችል ሁኔታዎች በሌሉበት በተጠቀሰዉ መልኩ መሰል ድርጊቶችን መሰይም የሚያመጣዉ የፖለቲካ እና የሕግ ትርጓሜ የተዘባ ያደርገዋል፡፡

ስለሆነም ከላይ በተቀመጠዉ መልኩ በአመዛኙ በመነሻነት ለመመልከት መሞከር የተሻለ ይሆናል፡፡